

## የኤሌትሪክ ሀይል፣ ጋዝና ውሀ ጠፍቷልን? እነዚህን እንዴት እንደገና ማስቀጠል እችላለሁ?

በእሳት አደጋው ጊዜ የኤሌትሪክ ሀይል፣ ጋዝና ውሀ ቆጣሪ ለደህንነት ሲባል በተመደበ የእሳት አደጋ ሀላፊ እንዲጠፉ ይፈለግ ይሆናል።

ዋስትና ገብተው ከሆነ የርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ እነዚህን አገልግሎቶች እንደገና ለማስቀጠል ማቀናጀት ይችላል። ዋስትና ካልገቡ ግን በራስዎ ለእያንዳንዱ አገልግሎት አቅራቢና ነጋዴ በመደወል የማስቀጠሉን ተግባር ያካሂዳሉ።

የርስዎ ኤሌትሪክ ሀይል፣ ጋዝና ውሀ ፍጆታ አቅራቢዎች ወደ ቤትዎ ባለሙያ ነጋዴ መጥቶ የተበላሸውን ማየትና ማንኛውንም ብልሽት ጠግኖ አገልግሎቱ እንደገና እንዲቀጠል ቅንጅት ይደረጋል።

## እዚህ ላይ የመገናኛ ብዙሀን ለምን አስፈለገ?

የመገናኛ ብዙሀን ብዙጊዜ በዜና ጋዜጣቸው ላይ ስለ እሳት ሪፖርት ያቀርባሉ። ሪፖርት አቅራቢው እርስዎን ቃለመጠይቅ ለማድረግ ከመጣ ታዲያ ከነሱ ጋር ለመነጋገር ስለመፈለግዎና አለመፈለግ የራስዎ ውሳኔ ይሆናል። በቃለመጠይቁ ተሳታፊ ለመሆን ከፈለጉ፣ በቅድሚያ ስለሚቀርበው የጥያቄ ዓይነት መወያየት ሲችሉ ታዲያ ምን እንደሚመጣ ግምት ይኖርዎታል። እንዲሁም የእሳት አደጋ ሀላፊ እንዲረዳዎ ወይም እንደ አቀነባባሪ ሆኖ እንዲረዳዎ መጠየቅ ይችላሉ።

በማንኛውም የቃለመጠየቅ ክፍል ላይ ደስተኛ ካልሆኑ፤ መቀጠል እንዳልፈለጉ ለሪፖርት አቅራቢው ማሳወቅ። የእሳት አደጋው መንስሂ ምክንያት እስካሁን ካልተገኘና በምርመራ ላይ ከሆነ፣ ከዜና ወኪሎች ጋር ምንም ውይይት አለማድረግ ይመረጣል።

## መምጣት ለሚችል የሆነ ሰው ማነጋገር እፈልጋለሁ?

በቤት እሳት አደጋ የሚከሰት አሰቃቂ ገጠመኝ ለአእምሮና ስሜታዊ ህመም ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህም ገጠመኝ የተለመደ ቢሆንም ነገር ግን ስለርስዎና ሌላው ቤተሰብዎ እንዴት መቋቋም እንዳለባችሁ ማሰብ ይገባል። በዚህን ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ከሆነ ሰው ማለት እንደ ቤተሰብ፣ ጓደኞች ወይም አማካሪ ጋር ተነጋግሮ እርዳታ ማግኘት አስፈላጊ ነው።

ለቤተሰብዎና ለርስዎ በFESA ስልክ አየር መልእክት በኩል ድጋፍ ሊያቀርብልዎ ይችላል። በተመደበ የእሳት አደጋ ሀላፊ አማካኝነት በአየር መልእክት ወደ ቤትዎ ደውሎ በደረሰብዎ አጣዳፊ የኽምሮ መረበሽ ድጋፍ በማቅረብ ታዲያ ለወደፊት እቅድ በማውጣት ላይ ሊረዳዎ ይችላል። በጊዜው በስልክ መስመር ላይ ሊረዱ የሚችሉ ብዛት ያላቸው ድርጅቶች ስላሉ መደወል ይችላሉ።

### የ24 ሰዓት ለድጋፍ ስልክ መደወያ ቁጥሮች:

**FESA Chaplain** **(08) 9485 7800**
(ይህ መልእክት የማስቀመጥ አገልግሎት ሲሆን ያለዎን መልእክት ማስቀመጥ ይገባል)

| | |
|---|---|
| **Crisis Care** | **(08) 9223 1111** |
| **The Samaritans** | **(08) 9381 5555** |
| **Lifeline** | **13 11 14** |

ለርስዎ የተመደበ እሳት አደጋ ሀላፊ
______________________________

እነሱም ከ ____________________ እሳት አደጋ ጣቢያ ሲሆኑ

በ ______________________________ የሥራ ፈረቃ ናቸው።

የስልክ ቁጥራቸው ______________________________

## በአሁን ጊዜ መከታተል ስላለብዎ የተነጋገሩትን በሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ የርስዎ እሳት አደጋ ሀላፊ ይረዳዎታል:

**ዋስትና ገብተው ከሆነ:**

- ☐ የርስዎን ኢንሹራንስ ኩባንያ ያነጋግሩ

**የርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ የሚያስተናግድዎት:**

- ☐ ለችግር ጊዜ መጠለያ
- ☐ ለችግር ጊዜ ምግብና ልብስ
- ☐ የደረሰውን ጉዳትና ብልሽት ለማጽዳት ለኩባንያው ማነጋገር
- ☐ የውሀ፣ ጋዝና ኤሌትሪክ አገልግሎት ለማስመርመርና እንደገና ለማስቀጠል

**የርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ስለሚከተለው ምክር ያቀርባል:**

- ☐ የቤትዎን ደህንነት ለማረጋገጥ ለማን እንደሚያነጋግሩ
- ☐ የኢንሹራንስ ገማች ገምጋሚ መቼ ወደ ቤትዎ እንደሚመጣ
- ☐ ቤትዎን ለማሰራት ነጋዴውን መቼ ማነጋገር እንደሚችሉ

**ቤትዎን ዋስትና ካላስገቡ ወይም የርስዎ ፖሊሲ የማያካትት ከሆነ ለማነጋገር:**

- ☐ ለመጠለያ፣ ምግብና ልብስ የድንገተኛ ወኪሎችን
- ☐ ለርስዎ ቤት ዋስትና ለሰጠ ኩባንያ
- ☐ ለመማክርትና የድጋፍ ድርጅቶች (የFESA Chaplain/ አየር መልእክትን ያካተተ)
- ☐ ጉዳቱንና ብልሽቱን ለሚያጸዳ ኩባንያ
- ☐ የተበላሸ ኤሌትሪክ ጠግኖ እንደገና ለሚቀጥል የኤሌትሪክ ባለሙያ
- ☐ የተበላሸ ጠግኖ ውሀና ጋዝ ለሚቀጥል የቧንቧ ሠራተኛ
- ☐ ቤትዎን ለሚጠግን ኩባንያ።

OCTOBER 2010

**የክህደት ቃል**
በዚህ መመሪያ ውስጥ ያለው መረጃ በእሳትና ድንገተኛ አገልግሎት ባለሥልጣን (FESA) በኩል እንደ ህዝባዊ አገልግሎት ሆኖ በፈቃደኝነት የቀረበ ነው። ይህ መመሪያ ዚዘጋጅ በጥሩ እምነትና በህትመት ጊዜ ትክክለኛና ታማኝ ከሆነ ምንጭ የተወሰደ ነው። ይሁን እንጂ የመረጃው ታማኝነትና ትክክለኛነት ዋስትና ላይኖረው ስለሚችል ታዲያ መረጃውን ተከትሎ ላልተደረገና ለሚከሰት ማንኛውም ተጨማሪ አንቀጽ ወይም ለተተወ ነገር ወይም ከነዚህ አንቀጽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ ለተጠቀሱ የ FESA ሃላፊነት እንደማይወስድ ቃል ይገባል። ይህ ጥራዝ ወረቀት እንደ መመሪያ ብቻ ለማገልገል ተብሎ የወጣ እንጂ አንባቢዎች ለራሳቸው ጉዳይ ነብስወከፍ ምክር በማግኘት የራሳቸውን ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው።

Government of Western Australia
Fire & Emergency Services Authority

FESA
Fire & Emergency Services Authority of Western Australia

# ቁርጭራጩን ማንሳት ...

## በቤትዎ ውስጥ እሳት ከተነሳ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚችሉ



amharic

Government of Western Australia
Fire & Emergency Services Authority

FESA
Fire & Emergency Services Authority of Western Australia

ቤትዎ በእሳት ከተጎዳ ወይም ከወደመ የመደንገጥና የመደናገር ስሜት ሊያድርብዎ ይችላል። እንዲሁም ምን እንደተፈጠረ ለማመን ሊያስቸግር ይችላል። ይህ የተለመደና በአጠቃላይ ከጊዜ በኋላ እነዚህ ስሜቶች ይጠፋሉ። በዚህን ጊዜ ወደ መደበኛ ሁኔታዎ ለመመለስ እንዲችሉ የሚረዱ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ነው።

ይህ ጥራዝ ወረቀት ሰለሚኖርዎ አማራጮች እንዲያውቁ ሲረዳዎ ይህም እንዴት ልብስ ማግኘት እንደሚችሉና በቤት ውስጥ መቆየት ካልቻሉ የት መሄድ እንዳለብዎ መወሰን አንደሚችሉ ነው። እንዲሁም በአካባቢው የተመደበው የእሳት ሀላፊ ሊረዳዎ ይችላል።

## ዛሬ ማታ የማድርበት ምንም ቦታ የለኝም። ታዲያ ለቤተሰቤና ለራሴ ምን ይደረጋል?

ቤትዎ በኢንሹራንስ ዋስትና ካለው በፖሊሲው መሰረት የድንገተኛ መጠለያ ለማግኘት የተካተተ ከሆነ ለርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ደውሎ ማነጋገር። ብዙጊዜ ከሥራ ውጭ የስልክ ቁጥሮች ይቀርባሉ። ቤቱን ኢንሹራንስ ዋስትና ካላስገቡት ታዲያ ከቤተሰብ ወይም ጓደኞች ጋር መቆየት ይቻል ይሆናል።

ለDepartment of Housing ማነጋገር ሌላው አማራጭ ሲሆን እነሱም ኪሳራ/ችግር ለደረሰበት መጠለያ እንዲያገኙ መርዳት ሲችሉ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ መኖሪያ ቤት ወይም በማህበረሰባት የኪሳራ/ችግር እንክብካቤ መስጫ መምሪያ በኩል እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።

**Department of Housing, Homeless Advisory Service:**
**በነጻ ለመደወል 1800 065 892**
(ከጥዋቱ 8am እስከ ከሰዓት በኋላ 5pm ከሰኞ እስከ ዓርብ)

**Department for Communities, Crisis Care:**
**(08) 9223 1111 ወይም በነጻ ለመደወል 1800 199 008**
(ቀን ወይም ማታ)

## እንዴት የእኔ ኢንሹራንስ ኩባንያ በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ ይሆናል?

የንብረቱ ባለቤት ከሆኑ በተቻለ ፍጥነት ለርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ማሳወቅ አለብዎ። የጉዳቱን ዋጋ ለመገመትና በስምምነት የክፍያ መጠን ለመወሰን የሚችል ተወካይ ይልካሉ።

የቤቱ ተከራይ ከሆኑና የቤት እቃ ኢንሹራንስ ዋስትና ካለው ስለ እሳት አደጋ ለቤቱ ባለንብረት ወይም አከራይ ድርጅት ከመናገር ባሻገር እርስዎ ለቤት እቃ ዋስትና ለገቡበት ኢንሹራንስ ኩባንያ መናገር አለብዎ።

## ኢንሹራንስ ከሌለኝስ ምን ይደረጋል?

ቤትዎን ለመጠገን በራስዎ ማቀናጀት ሲያስፈልግ ነገር ግን ቤተሰብ ወይም ጓደኞችን እንዲረድዎ ለመጠየቅ አለመዘንጋት ነው።

## ቤቴስ ለማሳደሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ ነውን?

የቤቱ ባለንብረት ከሆኑ የኢንሹራንስ ግምገማ ውጤት በሚጠብቁበት ጊዜ ለቤትዎ ደህንነት ማቀናጀቱ የራስዎ ሀላፊነት ነው። የርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ምክር ያቀርብልዎታል እንዲሁም የኢንሹራንስ ተወካይ የሚመጣ ከሆነ ታዲያ የቤትዎን ደህንነት ለመጠበቅ የኮንትራት ሠራተኛ ሊያቀናጁ ይችላሉ። የሆነ ጥያቄ ካለዎት ለአካባቢዎ ፖሊስ ያነጋግሩ።

አካባቢውን ክፍት አድርጎ በመተው ለበለጠ ጉዳት የሚያጋልጥ ከሆነ በState Emergency Service (SES) በኩል የዝናብ ሽፋንን በማስተካከልና የላላና የተላቀቀ ነገር ካለ እንዲታሰር ያደርጋል። ይህንን ለማቀናጀት ለተመደበ የእሳት ቃጠሎ ሀላፊ ወይም ለፖሊስ መኰንን መጠየቅ ወይም ለግዛት የድንገተኛ አገልግሎት (SES) በስልክ 132 500 ደውሎ ማነጋገር።



## በእሳቱ ሳቢያ ሁሉም ነገር ወድሟል። እንዴት እራሴን መመገብና ቤተሰቤን ማልበስ እችላለሁ?

ኢንሹራንስ ዋስትና ገብተው ከሆነ ምናልባት በርስዎ ፖሊሲ አማካኝነት የምግብና የልብስ እርዳታ ማቅረብ ካለባቸው ከርስዎ ኢንሹራን ኩባንያ ጋር ማረጋገጥ።

ኢንሹራንስ ዋስትና ካልገቡ ወይም ይህ በኢንሹራንሱ ላይ ካልተካተተ በDepartment for Child Protection ወይም በ Department for Communities Crisis Care በኩል የምግብ፣ የልብስ እርዳታ፣ የችግር ጊዜ መጠለያ እና ሌሎች አስፈላጊ ጠቃሚ ነገሮች እርዳታ ማቅረብ ይችላሉ።

**Department for Child Protection:**
**(08) 9222 2555, በነጻ ለመደወል 1800 622 258**
(ከጥዋቱ 8am እስከ ሰዓት በኋላ 5pm ከሰኞ እስከ ዓርብ)

**Department for Communities, Crisis Care:**
**(08) 9223 1111 ወይም በነጻ ለመደወል 1800 199 008**
(ቀን ወይም ማታ)

ለአንዳንድ የሚያስፈልግዎ ነገሮች ለማቅረብ የሚችሉ ሰዎች። እባክዎ ይህንን እንዲያቀናጅልዎ ለተመደበ የእሳት አደጋ ሀላፊ መጠየቅ ወይም በስልክ (08) 9485 7800 ደውሎ መልእክት በማስቀመጥ መጥራት።

## የግል እቃዎችን ማውጣት እችላለሁ?

በቤቱ የተወሰነ አካል በእሳት ያልወደመ ከሆነ እና በተመደበ የእሳት አደጋ ሀላፊ ወይም በእሳት መርማሪ ሀላፊ በኩል ወደ ቤት ስለመግባት የማያሰጋ ከተነገርዎ የሚከተሉትን እቃዎች ከፈለጉ ማውጣት ይችላሉ:

- መታወቂያ
- ክረዲት ካርድ
- የቸክ መጻፊያ ጥራዝ
- ህጋዊ የሆኑ ሰነዶች
- ስለ ኢንሹራንስ መረጃዎችን
- መድሃኒቶች
- የዓይን መነጽሮች
- የመስሚያ ወይም የግላዊ መገልገያ
- ጌጣጌጥ፣ የፎቶ አልበሞች፣ ዲቪድስ/DVD's
- ሌላ ጠቃሚ እቃዎች።

**ይሁን እንጂ ማንኛውንም እቃ ከማውጣትዎ በፊት ከርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ማጣራቱ የበለጠ ነው።**

## እሳቱ በቤቴ ላይ ብዙ ብልሽት አድርሷል። መቸ ነው የማጸዳው?

በአጠቃላይ እሳቱን ለማጥፋት የእሳት አጢፊዎች ሀይለኛ ግፊት ያለው ውሀ ይጠቀማሉ። እነሱም ጉዳቱን ለመቀነስ የተቻላቸውን ዓይነት ጥረት በማድረግና የቤተሰቡ እቃንና የቤት እቃዎችን ስለሚከላከሉ ስለዚህ በፍጥነት ወደ ቤትዎ ለመመለስ ይችላሉ።

እሳቱ በቤትዎ ውስጥ ላይ ጉዳት ካደረሰ ምናልባት አንዳንድ ጽዳት ያስፈልገዋል። የጽዳት ሥራው መቸ እንደሚጀመር ለማወቅ ከተመደበ እሳት አደጋ ሀላፊ፤ የእሳት መርማሪ ሀላፊ ወይም ከፖሊስ መኰንን ጋር ማጣራት። የምርመራ ወይም የዋጋ ግምት ሂደት እየተካሄደ ከሆነ ምናልባት የጽዳት ሥራን መጀመር የማይቻልበት አንዳንድ ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንዲሁም የንግድ አጽጅዎችን ፖሊሲው የሚፈቅድ ከሆነ ከርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ማጣራት።

## የእሳት መርመራ ሀላፊ የሥራ ድርሻ ምንድ ነው?

በእሳት አደጋው የተመደበ ሀላፊ የእሳቱን መንስሂ ምክንያት ማግኘት ካልቻለ ታዲያ ወደ የእሳት ምርመራ ሀላፊ መደወል ይችሉ ይሆናል። እንዲሁም በእሳት አደጋው የሆነ ሰው በጣም ከተጎዳ ወይም ከሞተ የፖሊስ መኰንን ይመጣል።

የቤትዎ እሳት አደጋ በምርመራ ላይ እያለ ስለደህንነቱ የሚያረጋግጥ ሃላፊነት የእሳት ምርመራ ሀላፊ ወይም የፖሊስ መኰንን ይሆናል። በቤትዎ ዙሪያ እንደ አጥር ለመከላከያ የቴፕ ክር ያደርጉበታል፤ ስለዚህ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ስለሚሆን ሰዎች ወደ ቤቱ እንዳይገቡ እና ለምርመራው ድርድር ስምምነት ላይ እንዲደርስ ሊረዳ ይችላል።

ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ወደ ቤትዎ ለመግባት ከፈለጉ፤ ታዲያ የእሳት ምርመራ ሀላፊ ወይም የፖሊስ መኰንን አብሮ መሄድ ይችላል። የምርመራ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቤትዎን በራስዎ እንዲቆጣጠሩት ይመለስልዎታል።

## የፖሊስ የቃጠሎ ቡድን ሥራ ድርሻ ምንድ ነው?

በእሳት ምርመራ ሀላፊ ከተጠየቀ ይህ ቡድን ይመጣል። ብዙጊዜ ከእሳት አደጋ አገልግሎት ጋር በተዛመደ ይሰራሉ፤ ይህም የእሳት መንስሂው አጠራጣሪ ከሆነ ወይም ሆን ተብሎ የተደረገ፣ መወሰን ካልተቻለ ወይም የሆነ ሰው ከሞተ የቃጠሎ ቡድን ይሄዳል።